የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ የካቲት ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 14
ADDIS ABABA 10th February 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፺፬/፪ሺ፫
ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ................................ገጽ ፭ሺ፯፻፭

## CONTENTS

Regulation No. 194/2010
National Metrology Institute Establishment Council of Ministers Regulation ...........................Page 5705

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፬/፪ሺ፫

## ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፬/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ስነ-ልክ" ማለት የአለካክ ሳይንስ ነው፤

፪/ "ሕጋዊ ስነ-ልክ" ማለት በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ልኬትን፣ የልኬት አሀዶችን፣ የመለኪያ መሣሪያዎችንና የልኬት ዘዴዎችን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚከናወን ተግባር ነው፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 194/2010

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL METROLOGY INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "National Metrology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 194/2010".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "metrology" means the science of measurement;

2/ "legal metrology" means verification of measurement, measurement units, measurement instruments and measurement methods performed by law enforcement bodies in accordance with requirements specified by the law;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.70

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O. Box 80,001

፲፪/ "የእርከን ተዋረድ ትስስር" ማለት የልኬት ውጤትን ወይም መደበኛ የመለኪያ መሣሪያ የልኬት መጠንን በሚመለከት የእርግጠኝነት መጠን ንጽጽሩ ከታወቀና አስተማማኝነቱ ከተመሰከረለት የማመሳከሪያ የልኬት መጠን ጋር በማነፃፀር ያላቸውን ልዩነትና አንድነት ለመወሰን እንዲቻል ቀጣይነት ባለው መንገድ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ትስስሩን መጠበቅ ነው፤

፲፫/ "እርግጠኛ ያለመሆን መጠን" ማለት ከልኬት ሥርዓቱ ውጤት ጋር በተያያዘ ለልኬት በቀረበው የተወሰነ መጠን በትክክል እንዳይገኝ አስተዋፆ የሚያደርጉ ጉዳዮች ተሰልተው የሚገኘው የልኬት ውጤት ነው፤

፲፬/ "የሳይንስ መሣሪያ" ማለት ለምርምርና ሥርፀት፣ ለትምህርትና ሥልጠና፣ ለጥራት ቁጥጥርና ፍተሻ፣ ለስነልክ ወይም ለሰው ወይም ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎቶች ሥራ ላይ የሚውል መሣሪያ ነው፤

፲፭/ "ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፲፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፯/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩቱ

### ፫. መቋቋም

፩/ ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

### ፭. ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ከዓለም ዓቀፍ ስነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ ብሄራዊ የስነ-ልክ ስርዓትን የመዘርጋትና በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማምጣት፤

፪/ የአገሪቱን ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችና የተመሰከረላቸውን የማመሳከሪያ ስረቶች ከዓለም አቀፍ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር ለማመሳከር፣ ለመጠበቅና ለማሰራጨት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፤

12/ "traceability chain" means the continual maintenance of national and international linkages of measurement traceability so as to determine the relationship between the reliability of measurement results or measurement result of formal measurement device and certified reference measurement results;

13/ "uncertainty" means a parameter, associated with the result of a measurement that could reasonably attribute not to obtain the expected result of the particular quantity subject to measurement;

14/ "scientific instrument" means a device used for research and development, education and training, quality control and inspection, metrology or diagnosis and treatment of human beings or animals;

15/ "Ministry" means the Ministry of Science and Technology;

16/ "State" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

17/ "person" means a natural or juridical person;

18/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## THE ETHIOPIAN NATIONAL METROLOGY INSTITUTE

### 3. Establishment

1/ the Ethiopian National Metrology Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

### 4. Head Office

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

### 5. Objectives

The Institute shall have the objectives to:

1/ develop national metrology system compatible with international metrology system and ensure technology transfer in the sector;

2/ establish and implement a system that enable to compare Ethiopian national measurement etalons and certified reference materials with international etalons and to maintain and disseminate them;

፫/ በስነ-ልክ ዘርፍ የትምህርትና የምርምር ተግባራትን የመደገፍ፤

፬/ የሳይንስ መሣሪያዎችን ጥገና ብሔራዊ አቅም መገንባትና የጥገና አገልግሎት የመስጠት፤

፭/ ለሳይንስ መሣሪያዎች ተጠቃሚዎች የቴክኒክ፣ የስልጠና፣ የምክርና የመረጃ አገልግሎቶችን በመስጠት ተግባሮቻቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ የመደገፍ።

## ፮. ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ዓለም አቀፍ የአሃዶች ሥርዓትን በማስተዋወቅና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው የልኬት መስፈሪያዎችን በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማስቻል በሥራ ላይ ያሉ ባህላዊ የመለኪያ መሣሪያዎችን ወደ ዘመናዊነት የማሸጋገር፤

፪/ ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችን የመወሰንና የመጠበቅ፤

፫/ ብሔራዊ የስነ-ልክ ላቦራቶሪ የማቋቋምና የካሊብሬሽን አገልግሎት የመስጠት፤

፬/ ለኢንዱስትሪው በስነ-ልክ ጽንሰ ሃሳብና የተግባር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት የራሳቸውን የውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶሪ እንዲያቋቁሙ እገዛ የማድረግ፤

፭/ የሌሎች ሀገሮችን ምርጥ ተሞክሮዎች መሠረት በማድረግ በስነ-ልክ ዘርፍ የትምህርት ካሪኩለም ቀረፃ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግና ምርምር የማካሄድ አቅምን በመገንባት ረገድ የዩኒቨርስቲዎችንና የምርምር ተቋማትን የማገዝ፤

፮/ በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን የልኬት አሃዶች፣ የአሃዶቹን ምልክቶችና ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችን በማሳተም ለሕዝብ የማሳወቅ፤

፯/ ስነ-ልክን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍ መድረክ የሀገሪቱን ጥቅም መወከልና ሀገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የመከታተል፤

፰/ ከሌሎች ብሄራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፍ የስነ-ልክ ተቋማት ጋር በሚደረግ የእርስ በርስ የካሊብሬሽን ውጤት ንፅፅር የካሊብሬሽን አገልግሎት አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ፤

፱/ ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር የተቀናጀ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመሥራት፤

፲/ ከዩኒቨርስቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር በዘርፉ ምርምር ማካሄድና የምርምር ውጤቶቹን ወደ ኢንዱስትሪዎች የማስረፅ፤

፲፩/ ስነ-ልክን የተመለከተ የሥርዓተ-ሰነድና መረጃ ማዕከል የማቋቋምና አገልግሎቱን የመስጠት፤

፲፪/ የህጋዊ ስነ-ልክ ሥራን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል አስፈላጊውን የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ የመስጠት፤

፲፫/ ስለሳይንስ መሣሪያዎች መረጣና ግዥ፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እንክብካቤ፣ ጥገናና አወጋገድ ለተጠቃሚዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

3/ support education and research activities in the field of metrology;

4/ build national capabilities for maintenance of scientific instruments and provide maintenance services;

5/ provide technical, training, consultancy and information services on scientific equipment with a view to supporting users to carry out their duties effectively.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ transform existing traditional measurement instruments into modernity through introducing international system of units and by enabling to use other acceptable measurement instruments in the country;

2/ determine and maintain national measurement etalons;

3/ establish national metrology laboratory and provide calibration services;

4/ support industries in establishing their own calibration laboratories through providing theoretical and practical training and consultancy on metrology;

5/ based on other countries best practices, provide support in building the capacities of universities and research institutions in curriculum designing and implementation process and conducting research in the field of metrology;

6/ publish and declare to the public measurement units to be used in the country, symbols of the measurement units and national measurement etalons;

7/ represent the country's interest in international forums regarding metrology and follow up the implementation of treaties to which Ethiopia is a party;

8/ participate in the calibration result inter comparison program with other national, regional and international metrology institutes intended to ensure the reliability of calibration services;

9/ work in cooperation with the relevant stakeholders to ensure the existence of an integrated support for strengthening the national quality infrastructure;

10/ conduct research in the field of metrology in collaboration with universities and research institutions and disseminate the results thereof to industries;

11/ establish a documentation and information center for the provision of metrology related information;

12/ provide the necessary technical and professional support so as to make the legal metrology activities effective;

13/ provide consultancy services to scientific equipment users on selection and acquisition, handling and use, maintenance, repair and disposal of scientific equipment;

፲፬/ ስለሳይንስ መሣሪያዎች ግዥ፣ አያያዝና አጠቃቀም፣ እንክብካቤ፣ ጥገናና አወጋገድ ለተጠቃሚዎች ስልጠና ይሰጣል፤

፲፭/ የሳይንስ መሣሪያዎች ተጠቃሚ ተቋማት የራሳቸው የሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ወርክሾፕ እንዲያቋቁሙ የሥልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ እና ለሚያሰለጥናቸው ባለሙያዎች የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

፲፮/ ለሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ወርክሾፖች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

፲፯/ ከተቋማት አቅም በላይ የሆኑ የሳይንስ መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎቶች መስጠት፤

፲፰/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

፲፱/ ዓላማውን በብቃት በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች አካሎች በውክልና የመስጠት፤

፳/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፳፩/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተዘረዘሩትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ኢንስቲትዩቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

14/ provide training to scientific equipment users on acquisition, handling and use, maintenance, repair and disposal of scientific equipment;

15/ support scientific instrument user institutions in establishing their own maintenance workshops through providing training and support; and issue certificates to trainees;

16/ verify the competency of scientific instruments maintenance workshops;

17/ provide maintenance services of scientific instruments which are beyond the capability of user institutions;

18/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate determined by the government;

19/ delegate part of its powers and duties to other organs where it finds it necessary for the effective implementation of its objectives;

20/ own property, inter into contract, sue and be sued in its own name;

21/ carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

7. **<u>Organization of the Institute</u>**

The Institute shall have:

1/ a Director General and, as necessary, a Deputy Director General to be appointed by the government, and

2/ the necessary staff.

8. **<u>Powers and Duties of the Director General</u>**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Agency in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees with rare skills, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare work programs and budgets of the Institute; and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the budget approval for the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

ረ) የኢንስቲትዩትን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፱. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲. የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፩. የልኬት አሃዶችና መሣሪያዎች**

በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ በኢንስቲትዩቱ ታትመው ከተገለጹት የልኬት አሃዶችና ምልክቶች ውጪ ሌሎች አሃዶችና ምልክቶች እንዲሁም ትክክለኛነታቸው አስተማማኝ ያልሆነ የልኬት መሣሪያዎች በሥራ ላይ እንዳይውሉ የመቆጣጠር ሥልጣን አግባብ ላላቸው የፌዴራልና የክልል ህግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ ተሰጥቷል፡፡

**፲፪. ብሄራዊ የመለኪያ ኢታሎኖች**

፩/ ከዓለም ዓቀፍ የአሀዶች ሥርዓት ጋር በተያያዘ ብሄራዊ የመለኪያ ኢታሎን የልኬት ውጤት በአገሪቱ ውስጥ የመጨረሻው ትክክለኛ የልኬት መጠን ሆኖ ይቆጠራል፡፡

፪/ ለማንኛውም የህጋዊ ሜትሮሎጂ ልኬት አገልግሎት የሚውል ብሄራዊ የመለኪያ ኢታሎን ያልሆነ የመለኪያ ኢታሎን፡-

ሀ) ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር የእርከን ተዋረድ ትስስሩን መጠበቅ ይኖርበታል፤ እና

ለ) ወቅቱን በጠበቀ መንገድ እውቅና ባለው የካሊብሬሽን ላቦራቶሪ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመለኪያ ኢታሎን እርግጠኛ ያለመሆን መጠን ሊኖረው ይገባል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተገለፁት የመለኪያ ኢታሎኖች ውጭ የሆኑ የመለኪያ ኢታሎኖች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የመቆጣጠር ሥልጣን አግባብ ላላቸው የፌዴራልና የክልል ሕግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ ተሰጥቷል፡፡

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

**9. Budget**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

**10. Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or auditors designated by him.

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**11. Measurement Units and Instruments**

The relevant federal and state regulatory bodies are hereby authorized to control the use of measurement units and symbols other than those declared by the Institute as well as unreliable measurement instruments.

**12. National Measurement Etalons**

1/ In relation to international system of units the measurement result of a national measurement etalon shall be considered as the highest level of accuracy measurement result in the country.

2/ Any non-national measurement etalon to be used for any legal metrology service shall:

a) maintain its traceability chain with one or more primary national measurement etalons; and

b) be calibrated timely by an accredited calibration laboratory.

3/ Any measurement etalon shall have stated uncertainty values.

4/ The relevant federal and state regulatory bodies are hereby authorized to control the use of measurement etalons other than those specified under sub-articles (1) and (2) of this Article.

